# “ፓርላማ አለመግባት ትክክለኛ ውሳኔ ነው” የሚለው መኢአድ በፓርላማ ያለው መቀመጫዬ ይቆጠርልኝ ማለቱ ታወቀ

የቀድሞው “ቅንጅት” አባል ፓርቲ የነበረውና በምርጫ 97 በመኢአድ/ቅንጅት ስም ካቀረባቸው ዕጩዎች ውስጥ ኢንጅነር ኃይሉን ጨምሮ 52 አባላት የፓርላማ መቀመጫ አሸናፊ መሆናቸው ይታወሳል። ይሁን እንጂ፣ ፓርቲው ፓርላማ አለመግባትን በመወሰኑ የተመረጡት አባላቱ በራሳቸው ውሳኔ ወደ ምክር ቤት ገብተው የፓርላማ ቡድን አቋቁመው ትግላቸውን ቀጥለው እስከ አሁን ድረስ ዘልቀዋል።

መኢአድ እስከ አሁንም ድረስ “ፓርላማ አለመግባት ትክክለኛ ውሳኔ ነው” ብሎ የሚያምን በመሆኑና ፓርላማ የገቡ አባላቱ ደግሞ የመኢአድን ውሳኔ በመጣስ ፓርላማ በመግባታቸው ከፓርቲያቸው ተለያይተዋል። ይሁን እንጂ፣ በፓርቲዎች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት ለፓርቲዎች የሚደረገው ድጎማም ሆነ የአየር ሰዓት ድልድል ቀመር ፓርቲዎች በፓርላማና በክልል ምክር ቤቶች ያላቸውን መቀመጫ መሰረት አድርጎ የሚከናወን በመሆኑ መኢአድ “በፓርላማ መቀመጫ አለኝ” የሚል ጥያቄ ለፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በማቅረቡ ም/ቤቱ መጋቢት 29 ቀን 2002 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ውይይት አድርጎበታል ሲል ከስፍራው የደረሰን መረጃ አመለከተ።

የዜና ምንጩ በላከልን መረጃ መሰረት፣ በጋራ ምክር ቤቱ የመኢአድ ተወካዮች የሆኑት አቶ ያዕቆብ ልኬ፣ ዶ/ር ታዲዮስ ቦጋለ እና አቶ አሰፋ ሀ/ወልድ “መኢአድ በፓርላማ መቀመጫ አለው። ይህም መቀመጫው ለገንዘብ ድጎማ እና ለሰዓት ክፍፍሉ ቀመር ግንዛቤ ውስጥ ሊገባለት ይገባል። ፓርላማው ለምርጫ ቦርድ በጻፈው ደብዳቤ ግን መኢአድ መቀመጫ እንዳለው ባለመግለጹ ይኽ ጉዳይ ሊታይልን ይገባል” የሚል ሃሳባቸውን በፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ አቅርበዋል።

በጋራ ምክር ቤቱ አባል የሆኑ ፓርቲዎችም በጉዳዩ ላይ በሰፊው የመከሩበት መሆኑን የዜና ምንጩ ጠቅሶ፣ “መኢአድ ፓርላማ መግባት ስህተት መሆኑን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በፓርቲው ሊቀ መንበር ጭምር እየገለጸ በፓርላማ መቀመጫ አለኝ ማለቱ ሁለቱ ሃሳብ አይጋጭም ወይ?” የሚል ጥያቄ መነሳቱንና በመኢአድ ተወካዮች በኩል ደግሞ “የፓርቲው ሊቀ መንበር እንደዚያ ቢሉም በመኢአድ ስም የተመረጡ አባላቱ በፓርላማ እስካሉ ድረስ የእነሱ መቀመጫ ለፓርቲው ሊቆጠር ይገባል” የሚል መከራከሪያ መቅረቡን የዜና ምንጩ አብራርቷል።

ይሁን እንጂ፣ የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላቱ በበኩላቸው “መኢአድ ‘ፓርላማ መግባት ትክክል ነው’ የሚል አቋም እስከሌለው ድረስ በራሳቸው ፍላጎት የገቡ አባላቱ የያዙት መቀመጫ ሊቆጠርለት አይገባም። መኢአድ በፓርላማ አባላት እንጂ በስሙ የሚታወቅ መቀመጫ የለውም። ይህንን የሚፈልግ ከሆነ በቅድሚያ ‘ፓርላማ መግባት

ተገቢ ነው። በራሳቸው ውሳኔ ፓርላማ የገቡ አባሎቹ የያዙት መቀመጫ ይቆጠርልኝ' የሚል ደብዳቤ ለምርጫ ቦርድ እና ለፓርላማው ይጻፍ" የሚል አስተያየት ሰንዝረዋል ሲል የዜና ምንጩ ጨምሮ ገልጿል።

በመጨረሻም፤ መኢአድ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባቱ "የፖለቲካም የህግም ጉዳዮችን ተመልክተን የውሳኔ ሃሳብ ይዘን እስከምንቀርብ ጊዜ ይሰጠን" የሚል ሃሳብ በፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ባሉ የመኢአድ ተወካዮች ቀርቦ ጉዳዩ በእንጥልጥል ላይ መቆሙን የዜና ምንጩ ገላጿል።